“. . .

ፍርሃት ከወረረህ፣ ቀሚሱን ልበሰው፣

ነጠላውን ደርብ፣ ታኮውን ተጫማው፣

ሊፒስቲክ ተቀባ፣ ኩሉንም ተኳለው፣

ቁጭ ብለህም ሺና፣ መቆምህን ተወው፣

ፈጥኖህ እንዲወስድህም፣ አምላክን ለምነው፣

በድንህ ቢንቀሳቀስ፣ ምንም አትጠቅመው።

. . .”

ወንድ መሆን ካማረህ (ግጥም ለወጣቱ)

አንተነህ (ከቶሮንቶ)

ከደብተራው (www.debteraw.com) ፣ አሲምባና (www.assimba.org)፣ ኢትዮላይን (www.ethioline.com) ድረ ገጽ ተለጥፎ ከተገኘው ግጥም የተወሰደ።

ሙሉውን ግጥም ላላገኛችሁ ከጽሁፉ መጨረሻ አባሪ ተደርጎ ተያይዟል።

# የትግል እመቤቶች ኸረ መላ በሉ

ግጥሙን ዘልቄ እንድገባ የገፋፋኝ ርዕሱ ነው። **"ወንድ መሆን ካማረህ"** ሲል። ስለ ፆታ መቀየር በግጥም መልክ የቀረበ አዝናኝ ግጥም ሊሆን ይችላል ብዬ ስጀምረው ልቤ እየተሸበረና ለሀገራችን ነፃነትና እኩልነት፣ ለዴሞክራሲያዊ መብት መከበር፣ ደማቸውን ያፈሰሱት አጥንታቸውን የከሰከሱት ባለ ቀሚስና ነጠላ ተላባሾች ጀግኖች እናቶቻችንና እህቶቻችን እየመጡብኝ አንብቤ እንደ ጨረስኩ የንዴት ይሁን፡ የቁጭት በከባዱ ተነፈስኩና ለማከብራቸውና ለምኮራባቸው እናቶቼና እህቶቼ ስል አምስት ጣቶቼን ከብዕሬ አገናኘሁ።

ከላይ የቀነጠብኩት የግጥም ስንኝ ሳነብ ከቅርቧ የት እንዳለች ያልታወቀችው ቀሚስ ለባሿ የቤት ሳይሆን የትግል እመቤቷ የኢሕአፓዋ አበራሽ በርታ  ጀምሮ የጥንቷ የዓድዋ ጀግና በተፈጥሮ ሕግ መሠረት ቁጭ ብላ ሽንታ ጠላት አሸኚዋ ጣይቱ ጀምሮ ያሉት ጀግኖች እህቶቻችንና እናቶቻችን መጡብኝና አይ ትምክህተኝነት አልኩ። በአብዛኛው የኢሕአፓን ልሳን ዴሞክራሲያን ጨምሮ የሚለጥፉትና አፍቃሪ ኢሕአፓ የሆኑት ድረ ገጾች (ደብተራው፣ አሲምባና ኢትዮላይንስ) ይዘውት ብቅ ያሉት ቆሮንቶ በአለ ነዋሪ ስም የቀረበ ግጥም ነው። (የጽሁፉ ማብቂያ ቀጥሎ ግጥሙ አባሪ ተደርጓል)።

የኢትዮጵያ ሴቶች ታሪክ የራሳቸው ብቻ ሳይሆን የዓለም ሴቶች የጀግንነት ታሪክ ተጋሪ በመሆናቸው ነው በየዓመቱ ማርች 08 የሴቶች ቀን የሚያከብሩት። በኢትዮጵያ የነፃነትና የዴሞክራሲ ትግል ታሪክ የሀገራችን ሴቶች የትግል ታሪክ አኩሪና ሁሌም የሚጠቀስና የሚተረክ ነው። ኢትዮጵያ አንድነቷን ጠብቃ በነፃነት ትኖር ዘንድ ሴቶች እናቶቻችንና እህቶቻችን ነጠላቸውን ታጥቀው በቀሚሳቸው ኮርተው ነው ዛሬ ያለችዋን ኢትዮጵያ ያቆዩን። በጦር ሜዳ ውሎ ከወንድ እኩል ተሰልፈው መስዋዕትነት ሲከፍሉ በተፈጥሮ ሕግ መሠረት ቁጭ ብለው እየሸኑ ነው። ተፈጥሮ የለገሰቻቸው ገጸ በረከት የጀግንነት መለኪያና ዓርማ ሆኖ በትምክህት ሲጻፍ ያውም በዛሬ ጊዜ የት ነው ያለነው ያሰኛል። "ከመምህሩ ደቀ መዝሙሩ" እንዲሉ ወይም "ከነገረኝ ደግሞ የነገረኝ" እንዲሉ እንዲህ ዓይነት በትምክህት የተሞላ ግጥም ከላይ በተጠቀሱት ድረ ገጾች ላይ መውጣቱ እጅጉን ያሳዝናል። ያሳፍራልም።

ኢሕአፓ ከመነሻው ጀምሮ ለሴቶች እኩልነትና መብት መከበር የታገለና ስለ ሴቶች እህቶቻችን የትግልና የጀግንነት ተጋድሎ ብዙ ያለ፣ የፃፈና ያስነበበ ነው። ዛሬ ስሙን ይዞ ሴትነትን ሰዳቢ ግጥም ሲወጣ፡ ሲፃፍበት እውነት እኛ ነበርን ያሰኛል። "ኸረ ኩሉን ማን ኳለሽ…" የተዘፈነላት እህታችን ውበቷን መግለጫ እንጂ ፈሪነቷን መመዘኛ መሆኑ ያሳዝናል።

ተፈጥሮአዊ ችሮታቸው ሳያግዳቸው ወጣት ሴቶች በመቶ የሚቆጠሩ ወንዶችን እየመሩ በዱር በገደሉ ድሎችን አስመዝግበዋል።  የአሲምባ ጀግኖችን እየመሩ በሜዳው ፍልሚያ ውስጥ አኩሪ ታሪክ ጽፈው ያለፉ የኢሕአፓ እመቤቶች ቀሚስ ለባሾች፣ ነጠላ ተከናናቢዎች፣ ዝናር ታጣቂዎች፣ ታግለው አታጋዮች፣ ሴትነታቸው የጀግንነት መስፈሪያ ሲሆን ያሳዝናል።

በጥንቱ የፊውዳሉ ሥርዓት ጀግንነት ለወንድነት የተሰጠ ይመስል ሴቶች እህቶቻችንን በተረቱም፡ በቤተሰብ ግንባታውም ዝቅ ማድረጉ ይቆም ዘንድ "የሴቶች ጥያቄ" ብለን የፃፍንለት፡ የታገልንለትና ስንት ደም የፈሰሰለት ዛሬም የድርጅቱ ተሟጋች ነን በሚሉ ድረ ገጾች "ሴትነት ፈሪነት" ተብሎ **"ወንድ መሆን ካማረህ"** ሲለጠፍ፣ ሲገጠም ኸረ የኢሕአፓ ያለህ ያሰኛል።

በዘመነ ፊውዳል "የወንድ ልጅ እናት ታጠቂ በገመድ ልጅሽን አሞራ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ" የሚለውን "የጀግኖች እናት ታጠቂ በገመድ ልጅሽን ጅብ እንጂ አይቀብረውም ዘመድ" በሚል ኢ.ሕ.አ.ፓ ሲቀይር እጅግ ትልቅ ትርጉም እንዳለውና ምን ያህል የሴቶች እህቶቻችንን የትግል አጋርነት እንዳንጸባረቀበት ገጣሚው ያውቁ ይሆን? ሴቶች እህቶቻችን የጀግና እናት ብቻ ሳይሆኑ ጀግንነትን አስመዝጋቢ መሆናቸው እንዴት ተሳናቸው? ሴቶች እህቶቻችን በኢ.ሕ.አ.ፓም ሆነ በተለያዩ ድርጅቶች ተሰልፈው መብታቸው ተከብሮ፣ ሚናቸው ታውቆ፣ ጀግንነታቸው ተደንቆ ታግለዋል ዛሬም እንዲሁ። በኢ.ሕ.አ.ፓ ዘመን እናቶች በከተማው ትግል ወቅት የደረጉት አስተዋጽዎ ቀሚስና ነጠላቸውን አላስረሳም።

የአሲምባዋ መዝገብነሽ፡ የአዲስ አበባዋ ዳሮ ነጋሽ ቀና ብለው ይህን ግጥም ቢያዩ ከቶ ምን ይሉ። ስመ ጥሩዋ የውስጥ አርበኛ ቀሚስ ለባሿ ሸዋረገድ ገድሌ እኮ ምን ተሰማሽ?

የሶስት ሺህ ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ ስንል መነሻችን የሴት ንግሥት ያላት በሀገራችን የመጀመሪያዋ ንግሥተ ሳባ እኮ ያታ ቀየረች? የቴጌ ጣይቱ ጀግንነት ሴትነቷን አስካደ ይሆን? የትላንቷ ሕፃን ሽብሬ ወንድ ሆነሽ ነው ወይስ ጀግና የፈሰሰው ደምሽ? የትግሉ እመቤቶች ኸረ አንድ በሉ!

ብዙ ማለት በተቻለ ብቻ በዚሁ ላብቃ። ለገጣሚዎቻችን፡ ለጸሐፊዎቻችን ብቻ ሳይሆን ለለጣፊዎቻችንም ልቦና ይስጥልን እያልኩኝ በቅርቡ ሰኔ 2004 ዓ.ም. ከታተመው የአቶ እንዳልካቸው ይርጉ (ቺኪ) የግጥም መድብል "ቅን ምኞት" ውስጥ "በግኛ ብናገር" በሚለው አስተያየቴን እቋጫለሁ።

## በግኛ ብናገር

አሁን እንዳለሁት የሰው ፍጡር ሁኜ

ሰውኛ እያወራሁ

እኔነቴን ይገኔ ከሰዎች እየኖርሁ

የሰው ልጅ መሆኔ ቢፈቅድ ፍጥረቴ

ጉሮሮዬ ስሎ ለስልሶ አንደበቴ

ልሳኔ ቢቀየር

በግኛ ብናገር

ባ

ብዬ

የማልፈው

እጅግ ብዙ ነበር።

ታህሳስ 09 ቀን 2005 ዓ.ም.

ጣይቱ

አባሪ

## ወንድ መሆን ካማረህ (ግጥም ለወጣቱ)

### አንተነህ (ከቶሮንቶ)

አንድ ሕይወት አለህ፣ አንድ ሞት አላቸው፣
ገዝግዘው ሲገድሉህ፣ ምነው ዝም አልካቸው?!

ወጣቷ እህቴ፣ ጀግንነት ያባትሽ፣
ትዳር የተፈጥሮ፣ መሻት መፈለግሽ፣
ወንድ ሁሉ ወንድ አይደል፣ ምክር ልለግስሽ፣
ጀግናውን ከፈለግሽ፣ ኢሕአፓን ልዳርሽ።

ፍርሃት ከወረረህ፣ ቀሚሱን ልበሰው፣
ነጠላውን ደርብ፣ ታኮውን ተጫማው፣
ሊፒስቲክ ተቀባ፣ ኩሉንም ተኳለው፣
ቁጭ ብለህም ሺና፣ መቆምህን ተወው፣
ፈጥኖህ እንዲወስድህም፣ አምላክን ለምነው፣
በድንህ ቢንቀሳቀስ፣ ምንም አትጠቅመው።

እያወክ መተኛት፣ ዝም ብለህ መጋደም፣
ሀገርህ ስትሸጥ፣ ሃይማኖት ሲከለስ፣ ገዳማት ሲወድም፣
ህግ በሌለበት፣ ሀብት ለማፍራት መድከም፣
የጨው ገደል ሲናድ፣ ለትርፍ እሽቅድድም፣
ምንም አላዝንልህ፣ አብረሃቸው ውደም!

መነሣት ከፈለግህ፣ ታሪክህን ማደስ፣

ይጠበቅብሃል፣ ብድርን መመለስ፣

ባንዳውንም ማክሰም፣ ወያኔን መደቆስ፣

ሃገርህን ማዳን፣ ክብርህን ማስመለስ፣

ሕዝብህን መታደግ፣ ጠላት ማተራመስ፣

በያም፣ በፍስኩ፣ ወያኔን ብላና፣ "ቼ!" ብለህ ተቀደስ።

ወንድነትህን መልስ፣ ወንድ መሆን ካማረህ፣

ከበድን መላቀቅ፣ ትንሣኤንም ከሻህ፣

ኢ.ሕአፓን አማክረው፣ ጀግናውን ጠይቀው፣ ምስጢሩን ይንገርህ።

ሃገርህን ውደድ፣ ሕዝብህን አስቀድም፣ መብትህንም ንጠቅ፣

ቅንጣቢ አይመርህ፣ ጠላትህንም ለይ፣ ወዳጅህን እወቅ፣

ባንዶችን ማርከሻ፣ ለወያኔዎች ጠንቅ፣

ኢ.ወክንድ ጠበሉ፣ በየቦታው ይፍለቅ!

አንተም ተጠመቀው፣ ልክፍትህም ይልቀቅ!

ይልቀቅ ፍርሃትህ፣ ወንድ ሁን እንደገና፣

ጠበሉን ተጋተው፣ ለመፍትሄ ፍውስና፣

ቅዳሴ ዜማውም፣ ኢ.ሕአፓ ነውና!